Monthly Newsletter Vol 16 No.6



**ECSU to Launch ICSMIS**

**An Increase in the Speed of Connection**

JAN 2020

# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY

BUILDING CAPACITES IN THE PUBLIC SECTOR

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ



## ECSU WOLISO CAMPUS ORGANIZES TRAINING



**ቆይታ ከስልጥናና ማማከር ዘርፍ ም/ፕሬዚደንት**

**ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም**



PRINTED BY
International & Public Relations Directorate

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content

ECSU to Launch ICSMIS — 1

ECSU Woliso Campus Organizes Training — 2

An Increase in the Speed of Connection — 3

ቆይታ ከስልጥናና ማማከር ዘርፍ ም/ፕሬዚደንት — 4

ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም — 7

Editor In -Chife
Wondimu Moges

Editors
Wondimu Moges
Tariku Ayano
Anteneh Demisse

Photos
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

ግራፊክስ Design
Dereje Tesfaye

**PRINTED BY**
International & Public Relations Directorate

ECSU
International & Public Relations Directorate
Tel.0116462887
0116463015
E-mail;IPRD@ecsu.edu.et/
Po.box 5648
website;www.ecsu.edu.et
FM RADIO 100.5 MHz

# ECSU TO LAUNCH ICSMIS

Ethiopian Civil Service University Human Resource Management and Development Directoratein collaboration with Ethiopian Civil Service Commission trained ECSU staffs, directors and administrators on Integrated Civil Service Management Information System (ICSMIS) from 03 to07 February 2020 at Hidasse Hall. The training was given in four categories and more than three hundred seventy staff members participated.







On the training, the overall operation of the Integrated Civil Service Management InformationSystem and technical issues on how to use the system were presented by the trainer in detailand the trainees were informed that ECSU has been prepared to launch Integrated Civil Service Management Information System (ICSMIS) in the near future by the university Human Resource Management and Development Directorate.

Integrated Civil Service Management Information System (ICSMIS) is a system that is developed to modernize information saving system on human resource management and related activities by changing the manual system into a system based on a data base. By using this system employees can apply for annual leave, present their complaints, follow up their status,appeal for administration court etc.





# ECSU Woliso Campus Organizes Training

ECSU Training and Consultancy Division of Woliso Campus, organized a two days training toWoliso City Administration officials and zonal administration workers to empower the leaders and employees under the theme-"Honoring creativity and mind setting" from 31 January to 1 February at Woliso Campus of the university.




**Dr Wagari Negari**
*Vice President of training and consultancy division*

Dr Wagari Negari ,Vice President of training and consultancy division , said this is the beginning of our work at woliso campus and today we give the first training to the officials and employees on Honoring creativity and Mind setting. When the campus fully started the work,we give further training to the nearby zones employees on different topics to build their capacity.Surly in the nearby future we will fully start the training he added.



The trainees also said they are delighted that ECSU opened the campus at Woliso City and thanked the University .Besides, the training is very important and help them in developing their skill and knowledge. They also asked the campus to continue giving trainingon a variety of topics in the future. The training was given by Dr Waqgari Negari .



Ato Niguse Diriba, Director of ECSU Woliso Campus, said today is our startup training; webegin by giving training for more than 80 female employees and zonal officials. We will be strengthened in the future of the campus as a whole, and the training will benefit zonal professionals and leaders to build their capacity and grow them. We will also continue to train more employees in the future and planned to work with Woliso Administration in different areas to foster stronger collaboration he added.

He also requested the trainees to fully and actively participate on the training and make it a two way process by sharing their knowledge and experiences during the training time. Finally he expressed his hope that the Campus will start its career completely with in short period of time.





# An Increase in the Speed of Connection


ECSU significantly rose its internet speeds from 300 megabits per second (Mbps) to 1000mbps starting January 2020.

Ato Yitbarek Ibrahim, Information Communication Directorate Director, said that the internet speed is an important element in the overall educational activity. So this increment of the internet speed helps the university community to browse different sites rapidly and adapt the knowledge and information to the best of daily activities in the form of education, research, training consultancy services. "So we aspire to enhance the coverage and speed of internet services to the University community," said Ato Yitbarek.

The speed of the internet connection is measured in Mbps and the increment of the speed can increase the uploading and down loading data. According to Ato yitbarek, the current expansion has increased the speed more than threefold of what existed before.







# ቆይታ ከስልጥናና ማማከር ዘርፍ ም/ፕሬዚደንት

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም ለመገንባት በመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ፒኤች ዲ ደረጃ በማሰልጠን ላይ መሆኑ ይታወቃል ። ከእነዚህ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች በተጨማሪም በስልጥናና ማማከር ዘርፍ አመካይነት የተለያዩ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችና የማማከር አገልግሎት መርሀ ግብሮች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የፐብሊክ ሰርቫንቱን አቅም ለመገንባት እየሰራ ይገኛል። በእነዚህ መርሀ ግብሮችም ከፈጻሚ ባለሙያዎች ጀምሮ እስከ የስራ ኃላፊዎች ድረስ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፣ በመሰራትም ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅትም የስልጠናና የማማከር መርሀ ግብሩን ለማዘመንና አገልግሎቱን በስፋት ለመስጠት በማቀድ ዘርፉ የስልጠና ማዕከላትን በማደራጀት እና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን ይህን አስመልክቶ እየተሰሩ ስላሉ ተግባራት ከዘርፉ ምክትል ፕሬዚደንት ከዶ/ር ዋቅጋሪ ነገሪ ጋር አጭር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- በመጀመሪያ ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆኖ ከልብ እናመሰግናለን።***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** እኔም እንግዳችሁ እንድሆን ስለጋበዛችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛነት ከሚሰጠው የትምህርት መርሀ ግብር በተጨማሪ በምክትል ፕሬዚደንት የሚመራ የስልጠናና የማማከር ዘርፍ በመክፈት ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ መሆኑ ይታወቃል። የዘርፉ መመስረት አስፋለጊነትና የተቋቋመበትን ዓላማ ቢያስረዱን።***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** ይህ የስልጠናና የማማከር ዘርፍ በአሁኑ ወቅት እንደ ዘርፍ በአዲስ መልክ ይደራጅ እንጂ የስልጠናና የማማከር ፕሮግራሙ ቀድሞም ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ጀምሮ የነበረ ፕሮግራም ነው። ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት የአቅም ግንበታ ማዕከል / Center for Professional Development/ በመባል ነበር የስልጠናና ማማከር ስራው የተጀመረው። በወቅቱ በረጃጅም መርሀግብሮች የሚሰጡት የትምህርቶች መስኮችን በአጫጭር የስልጠናፕሮግራም ለመስጠት በማሰብ መርሀግብሩ ተጀመረ። በማዕከል ደረጃ ተግባራዊ በሆነ ስልጠናም አስተሳሰብን፣ እውቀትንና ክህሎትን ማሳደግ ላይ በማተኮር በአጫጭር ስልጠናዎችና በማማከር አገልግሎት ሲቪል ሰርቪሱን መገንባትና ለውጥ ለማምጣት በስፋት ሲሰራ ቆይቷል።

ከዚያም በመቀጠል ማዕከሉ በማደግ የሲቪል ሰርቪስ የሪፎርም ፕሮግራም እየተዘጋጀ ሲመጣ የሀገሪቱን የለውጥ መንፈስ በመከተል Center for Professional Development የሚለው Center for Civil Service Leadership and Management Development ተብሎ በመሰየም የሲቪል ሰርቪስ የሪፎርም ፕሮግራምን አስራ አራት ንዑስ ፕሮግራም ፓኬጆች ተቀርጸው ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል። ከእነዚህ መካከል የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እና ሌሎችም ማለትም የህግ ልማትን ፣ የከተማ ልማትን፣ የባለብዙ ዘርፍን አካቶ ስልጠናዎችን ሲሰጥበት ቆይቷል። ከዚያም በመቀጠልና እድገቱን በማፋጠን Center for Leadership and Management Development ለመሆን በቃ። ነገር ግን የቢፒአር ትግበራን ተከትሎ ስራዎችን እንደገና በሚደራጁበት ወቅት አጫጭር ስልጠናዎቹ የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች አካል በመሆናቸው በ Institute of Public Management and Development Studies ስር ተካተው ስልጠናዎቹ እንዲታጠፉ ተደረገ። በዚህ ጊዜ የስልጠናና ማማከሩ ተግባር ከትምህርት ስራው ጋር በመደበላለቁ የተነሳ ስራው ተደብቆ መቆየቱና በመዳከሙ የተነሳ እንዲሁ የስልጠና ማማከር ስራ የራሱ የሆነ ባህሪ እንዳለው በመገንዘብ ከኢኒስቲትዩቱ ተለይቶ እራሱን በመቻል ከአምስት አመት በፊት እንደዘርፍ እንዲቋቋም ተደረገ እንጂ የስልጠናና ማማከር ስራው ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረትም የነበረ መርሀ ግብር ነው።

አስፈላጊነቱን በተመለከተም ዘርፉ እንደሀገር የሚኖረው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው። የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትን ብንመለከት በርካታ የማሰልጠኛ ተቋማት አሏቸው። በዚህ ረገድ እንደሀገር ወደኋላ ቀርተናል ማለት ይቻላል። እኔም በጎበኘዋቸው ሀገራትም የተገነዘብኩት ይህንኑ ጉዳይ ነው። አሁን የእነዚያን ሀገራት ተሞክሮ በመቀመርና ከእኛ ሁኔታ ጋር በማላመድ እና ራሳችንን ተወዳዳሪ በማድረግ ሂደት ላይ እንገኛለን። በርካታ ሀገሮችም የሲቪል ሰርቪሳቸውን አቅም የገነቡት በረጃጅም የትምህርት መርሀ ግብሮች ብቻ ሳይሆን በስልጠናና በማማከር አገልግሎትም ነው። እነዚህ የስልጠናና ማማከር ስራዎች በብዙ መልኩ ሙያዊ ክህሎቶችን ወደ ሰው ልቦና ውስጥ የሚያሰርፁ፣ አገልግሎት

አሰጣጡን የሚያሳልጡና የሚያዳብሩ ናቸው። ስለዚህ የዚህ ዘርፍ አስፈላጊነት በእጅጉ ከፍተኛ ነው።

***ዓ/ሀ/ግ/ማ/ዳ:- የስልጠናና ማማከር ዘርፍ በስካሁኑ ሂደት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹን ቢጠቅሱልን።***



**ከዶ/ር ዋቅጋሪ ነገሪ**
የስልጠናና የማማከር ከዘርፉ ምክትል ፕሬዚደንት

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** በመጀመሪያ ደረጃ ዩኒቨርሲቲው በስልጠናና ማማከር ያልደረሰባቸው የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት መጠን እምብዛም አይደለም ። በዚህ አገልግሎት አብዛኛውን ተቋማት አዳርሷል ለማለት ይቻላል። በምን ደረሰ? ተብሎ ቢጠየቅ በሪፎርም ፕሮግራሞች፣ በቢፒአር ፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ እና ቢኤስ ሲን ለማስተግበር ሙሉ በሚባል ደረጃ የፐብሊክ ሴክተሮች ጋር ሊደርስ ችሏል። በዚያን ጊዜ በወቅቱ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ከሚባለው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመሆን በጋራ ግብረ ኃይል አሰማርተን ስንሰራ ነበር። የተለያዩ አቅም ያላቸውን አማካሪዎች ከተለያዩ ተቋማት ወደእኛ በማምጣትና በልዩ መልክ በማሰልጠን አሰማርተን ተደራሽ ሆነናል። ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ሁሉ የስልጠናና ማማከር ዘርፍ በርካታ ስራዎችን አከናውኗል።

አሁን ባለንበት ሁኔታ አቅማችን ውስን ቢሆንም እስካሁን ወደእኛ እየመጡና እኛም ወደእነርሱ በመሄድ ያሰለጠናቸው ሰልጣኞች በቁጥር ብናስቀምጥ ከአንድ መቶ ሰባ ሺህ በላይ የሆኑ፣ ከመጀመሪያው እርከን ጀምሮ እስከ ከፍተኛው እርከን ያሉ ሲቪል ሰርቫንቶችን አሰልጥነናል። ነገር ግን እንደ ሀገር ሲታይ ይህ በቂ ነው ለማለት አያስደፍርም ። የሀገራችን ፐብሊክ ሰርቪስ አቅም ግንባታ ሲታይ ደግሞ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና በአለም ባንክ በኩልም በ2017 ዓ.ም በተደረገው ዳሰሳ በሀገር ደረጃ የተቋቋሙ የስልጠናና የማማከር ተቋማት በርካታ ስራዎችን ቢሰሩም በበቂ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸውን ያመለክታል። እኛም ባደረግነው ወርክሾፕ በርካታ አካላት ጋር አለመድረሳችንንና የተፈለገውን ያህል አቅም አለመገንባቱን ለመገንዘብ ችለናል። ይህን ክፍተት በመሙላትም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመሆን የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ዕቅድ ይዘናል።

***ዓ/ሀ/ግ/ማ/ዳ:- ዩኒቨርሲቲው አገልግሎቱን ለማሻሻል ከያዛቸው ውጥኖች ውስጥ አንዱ ይህ ዘርፍ ነው። ለመሆኑ በዘርፉ እየተደረጉ ያሉ ለውጦች ምን ምን ናቸው ?***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ :-** በዩኒቨርሲቲው በዚህ ዘርፍ ላይ ብዙ ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ እየተሰራ ነው። የሚሰሩት ስራዎችም በሰው ሀብት ልማት፣ በብዛትና በጥራት የሰው ሀብትን አቅም ለመገንባት፣ ከዘመነው ዓለም ጋር አብሮ የሚሄድ አስተሳሰብና ክህሎት እንዲዳብር እየሰራን እንገኛለን። የአሰልጣኞችና የአማካሪዎችን አቅም ለመገንባት በስፋት እየሰራን ነው። በዚህ ረገድ ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ነን። ለዚህም ቀዳሚው የሚሆነው የአስተሳሰብ ልማት ላይ ያተኮረ ስልጠና ነው። በስልጠናውም ራሳችንን እየፈተሽን፣ ያለንንና የሚጎድለንን በመለየት እና የቡድን ስሜታችንን በማሳደግ ለመልማት ያለንን ድንበር የማስፋት ስራ እየሰራን እንገኛለን። ከሰው ሀብቱ በተጨማሪም በፋሲሊቲ ላይም ተወዳዳሪ ለመሆን በርካታ ስራዎች በመራት ላይ ናቸው። የስልጠና ክፍሎቻችንን ስማርት እንዲሆኑ እያደረግን ነው። ማስታወቂያዎችም ዘመናዊ በሆነ መልኩ እንዲተላለፉ ሳይንኔጅ ተክለናል። ስለዚህ ሁሉን አቀፍ የሆነ፣ ጥራት ያለው፣ የመልማትና የማሳደድ ስራ ይዘናል። የዘርፋችንም መርህ ለጥራት ቅድሚያ መስጠት ነው። ይህን በማድረግ ነው በ2017 ተወዳደሪ መሆንና የልዕቀት ማዕከል ለመሆን ያስቀመጥነውን ግብ ማሳካት የምንችለው። በሀገር ደረጃም ለሌሎች የስልጠና ተቋማት እንደምሳሌ ለመሆንም ነው እየሰራን ያለነው። ጥራታችንን ለማሳደግም አይ ኤስ ኦ ከሚባለው ተቋም ጋር ውል ገብተን ጥራታችንን በመገምገም የጥራት ሰርቲፊኬት ለማግኘት እየሰራን እንገኛለን። ይህ ደግሞ ከሀገር ውስጥ በተጨማሪ በውጪ ሀገራት ዘንድም ተፈላጊነታችንን የሚጨምር ይሆናል።

***ዓ/ሀ/ግ/ማ/ዳ:- በዘርፉ የሚሰጡ ስልጠናዎችን በስፋት ከመስጠትና ተደራሽነት ከማስፋት አንጻርስ ምን ስራ እየተሰራ ይገኛል?***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** በየወቅቱ የምናሰለጥነው የሲቪል ሰርቫንት ቁጥር በየጊዜው እያሳደግን መጥተናል። የዘንድሮ ዓመት እንኳን ብንመለከት አስር ሺህ ሰልጣኞችን ተቀብለን አሰልጥነናል። ይህም በየአመቱ እየጨመረ የመጣ ሲሆን አሁንም እየጨመረ የሚሄድ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ፐብሊክ ሴክተሩ ያለበት ስፍራ ድረስ በመሄድና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋርም በመመካከር የመጣ ነው። በአሁኑ ሰዓት ፐብሊክ ሴክተሩ የስልጠናና የማማከር

አገልግሎት ያለውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ በመገንዘቡና ለዚህ በስፋት በተሰራው ስራ የመጣ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ሌላው ደንበኞቻችን ባሉበት ቦታ በመሄድ ስልጠና መስጠት መጀመራችን በርካታ ሰልጠኞች ዘንድ እንድንደርስ አስችሎናል፡፡ ምንም እንኳን የተገኘው ግብረ መልስ አጥጋቢ ባይሆንም የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ልዩ ችግር ያለባቸውን ሴቶችን በቦታቸው ሄደን ለማሰልጠን በደብዳቤም በስልክም ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት ጥሪ አድርገናል፡፡ ይህ በራሱ አንድ የጨመረልን ነገር አለ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በየሲቪል ሰርቪስ ተቋማቱ የተለያዩ ሰዎችን እንደተወካይ የያዝን ሲሆን ከእነርሱ ጋር እየተነጋገርን አዳዲስ ነገሮች ሲመጡ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት ጀምረናል፡፡ በወሊሶ ላይ እየተሰራ ያለው የስልጠና ማዕከል ከዞኑ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮና የከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ለ 80 ሴቶችና ከ80 ለሚበልጡ አመራሮች ተግባራዊ የሆነ ስልጠና ለመስጠት እየሰራን ነው፡፡ ስልጠናውም በአስተሳሰብና በስራ ፈጠራ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ስልጠናውን መስጠት ብቻም ሳይሆን ስልጠናው የተሰጣቸው ሴቶች ተግባራዊ በሆነ ሁኔታ ስራን ፈጥረው ተጨባጭ የሆነ ውጤት ይዘን መመለስ እንዳለብን አቅደን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን፡፡ ለዚህም አስፈላጊው ግብዐት በመደራጀት ላይ በመሆኑ ስልጠናው በጥቂት ጊዜያት ውስጥ የሚጀመር ይሆናል፡፡ ይህን ስልጠና ተግባራዊ ስናደርግ የስልጠና ፈላጊዎቻችን ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ በዚህን ጊዜ የሚመጣውን ጫና ለመቋቋም አሁን አቅማችንን በስፋትም በጥራትም እየገነባን እንገኛለን፡፡ በወሊሶ ብቻ ሳንገደብም በሁሉም አቅጣጫ ተደራሽነታችንን ለማስፋት እንሰራለን፡፡

በሌላ በኩም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመሆን ብቃትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ( Competency Based Training ) ከባለፈው ሐምሌ ወር አንስቶ ጀምረናል፡፡ ስልጠናውንም ለአሰልጣኞቻችንና አማካሪዎቻችን ሰጥተናል፡፡ የስልጠና ማቴሪያሎችንም ማዘጋጀት ጀምረናል፡፡ ከኮሚሽን ጋር በመሆን ብቃትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ፍላጎትን የመለየት ስራ ተጀምሯል፡፡ ስልጠናው የሚሰጥበት የመግባቢያ ሰነድም ተፈራርመናል፡፡ ይህ ብቃትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ትልቅ ፋይዳ ያለው ስልጠና ነው፡፡ ከተለመደው አሰራር ወጣ ብለን በሌላ መንገድ እንድናይና እንድንሰራ የሚያደርገን አሰራር ነው፡፡በቀደመው አሰራር ሰልጣኞች ወደስልጠና ሲገቡም ሆነ ሲወጡ የሚሰጣቸው ፈተና አልነበረም፡፡ በዚህ ብቃትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ሰልጠኞች ወደስልጠና ሲመጡ ያላቸው ብቃት ለመለየት ፈተና ይሰጣቸዋል፤ በመቀጠልም ስልጠናውን በሚወስዱበት ጊዜ ይፈተናሉ፤ ስልጠናውን አጠናቀው በሚወጡበት ጊዜም ብቃታቻው ተመዝኖና ተፈትነው ሰርቲፋይድ ሆነው ነው የሚወጡት፡፡ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡትንም ዝቅተኛ ውጤት ማምጣታቸውን ገልጸን እንጽፋለን፡፡ መካከለኛ ከሆነ መካከለኛ፣ ከፍተኛ ውጤት ያመጡትንም ከፍተኛ ውጤት ማምጣታቸውን ጠቅሰን መጻፋችን በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የት ጋር ክፍተት እንዳለ በመለየት በምን መስክ ስልጠናንም ሆነ የማማከር አገልግሎት መስጠት እንደሚያስፈልግ ለመለየት ያስችላል፡፡

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- ዘርፉ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር እንደሚሰራ ይታወቃል፡፡ በዋናነት ከየትኞቹ ተቋማት ጋር በስፋት ይሰራል ? የሚሰራባቸውስ መስኮችስ ምን ምንድን ናቸው?***

***ዶ/ር ዋቅጋሪ:-*** እንደ ዘርፍ ከበርካታ ተቋማት ጋር በትብብር እንሰራለን፡፡ ዋና ዋናዎችን ለመጥቀስ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዝ ይሆናል፡፡ በከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ዝግጅት፣ በከተሞች ዙርያ በሚሰጡ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ በስፋት እንሰራለን፡፡ ዩኒቨርሲቲው የልዕቀት ማዕከል ይሆንበታል ከተባሉ ስራዎች አንዱ የከተማ ልማት በመሆኑ በመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር የሚሰጠው ትምህርት እንዳለ ሆኖ በስልጠናው ረገድ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በስፋት በመስራት ላይ እንገኛለን፡፡ ከአማራ፣ ቤኒሻንጉል፣ ከጋምቤላ፣ ከደቡብ ክልሎች ጋርም በከተሞች ላይ ሰፋፊ ስራዎችን በጋራ እየሰራን ነው፡፡

ሌላው በሴቶች ዙርያ በባለ ብዙ ዘርፍ አማካይነት ከሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር ጋር በስፋት እየሰራን ነው፡፡ በማማከር ፣ የፖሊሲ ዶክመንቶችን በመተቸት፣ ስልጠና በመስጠት እና በመሳሰሉት ላይ በሴቶች ጉዳይ ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በስፋት እየሰራን ነው፡፡

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋርም የረጅም ጊዜ ስምምነቶችን በመፈራረም የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት አብረን እየሰራን ነው ያለነው፡፡ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋርም የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በስፋት እየሰራን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር እየሰራን እንገኛለን፡፡ በቅርቡ ሶስት ሺህ የጉምሩክ አስተላላፊዎችን ለማሰልጠን በተፈራረምነው ስምምነት መሰረት በመጀመሪያው ዙር አምስት መቶ ሰልጣኞችን አሰልጥነናል፡ ፡ ሁለተኛ ዙር ስልጠናም እየተሰጠ ነው፡፡ በውላችን መሰረትም በዚህ ዓመት ሶስት ሺህ ሰልጣኞችን እናሰለጥናለን፡፡ በዚህ ስልጠና ላይ የሚሳተፉትም ከሁሉም ክልሎችና የሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች / ቀበሌዎች/ የሚመጡ ናቸው፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ከሁሉም ክልሎችና ወረዳዎች ነው ሰብስቦ የሚያመጣው፡፡ የጉምሩክ ኮሚሽንም ፣ ገቢዎች ሚኒስቴርም፣ ከተማልማትና ቤቶች ሚኒስቴርም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ነው ሰልጣኞችን ሰብስበው የሚያመጡት፡፡ ስለዚህ ከሁሉም ክልልና ማህበረሰብ የሚመጡ ሰልጣኞች ናቸው በተቋማችን እየሰለጠኑ ያሉት፡፡

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- የእነዚህ ስልጠናዎች መሰጠት እንደሀገር ያበረከተው አስተዋጽኦ እና ያለውን ፋይዳቢ ገልጹልን፡፡ ስልጠናው ከተሰጠ በኋላስ የታለመለትን ውጤት ማስገኘቱን በምን ዓይነት አግባብ ነው የምትመዝኑት?***

***ዶ/ር ዋቅጋሪ:-*** ስልጠናው ከተሰጠ በኋላስ የታለመለትን ውጤት ማስገኘቱን በመከታተል ረገድ በተደራጀ መልኩ ባይሆንም ቀደም ሲልም ክትትል ይደረግ ነበር፡፡ ለምሳሌ በቢፒአር ትግበራ፣ በባላንስድ ስኮር ካርድ፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በአስተሳሰብ ላይ በተሰጡ ስልጠናዎች አተገባበር ላይ ሰፊ የሆነ ክትትል ሲደረግ ነበር፡፡ የክትትሉ

ውጤት እንደሚያሳየውም በርካታ ለውጦች ታይተዋል። በተለያዩ ተቋማት ላይ ባደረግነው ዳሰሳም እንደተጠበቀው ባይሆንም ስኬቶች መመዝገባቸውን ለመገንዘብ ችለናል። ነገር ግን በትግበራ ሂደት ውስጥ ውጤት እንደሚኖር ሁሉ ያልተሳኩልንም ነገሮች አሉ። እነዚህ ያልተሳኩ ነገሮች ደግሞ እንደ ትምህርት በመውሰድና ከእነርሱ ተምረን አዳዲስ ነገሮችን በማቀድና በመተግበር ላይ እንገኛለን። ክፍተት የሌለበት ስራ መስራት ስለማይቻል የሚታዩን ክፍተቶች በመሙላት ስራዎችን እየሰራን ነው። ሁል ጊዜ ስኬታማነት አይኖርም ።ሲቪል ሰርቪሱም ሆነ ሰራተኛው በዚህ ቅኝት ነው መሄድ ያለበት። ለጠንካራ ችግሮች ጠንካራ መፍትሔ በማምጣት ፣ ከሚገጥሙ ፈተናዎችና ተግዳሮቶች በመማር ጠንክሮ በመስራት ራዕይንና ተልዕኮን ማሳካት ቀዳሚው ተግባር ሊሆን ይገባል።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- እነዚህን ስልጠናዎች በመስጠቱ እንደሀገር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዳለ ሆኖ ለዩኒቨርሲቲው ያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው?***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** ይህ ዘርፍ የዩኒቨርሲቲው ራዕይ ማሳኪያ ሁለቱ አዕማዶችን ያካተተ ነው ። የዩኒቨርሲቲው ራዕይ በእነዚህና ሌሎችም አዕማዶች ስኬት ላይ የሚመሰረት ነው። የዚህ ዘርፍ ስኬታማነት የዩኒቨርሲቲው ራዕይ በትክክልና ወደሚፈለገው አቅጣጫ እየሄደ መሆኑን አመላካች ነው። በጥቅሉ ሲታይ ዩኒቨርሲቲው በዚህ ዘርፍ ዓላማውን እያሳካ ፤ ለሀገርም ትርጉም ያለው ስራ እየተሰራ ነው ማለት ነው። ይህ ስራ ደግሞ የሀገሪቱን አጠቃላይ ራዕይ ስኬት የሚያሳልጥ ይሆናል። ስለዚህ ዘርፉ በዩኒቨርሲቲው ራዕይ ስኬትም ሆነ በሀገሪቷ የፐብሊክ ሰርቪስ አቅም ግንባታ ስኬት ላይ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

ሌላው በፋይናንስ ደረጃ ያለውን ብንመለከት ዘርፉ ለዩኒቨርሲቲው ትልቅ ገቢ እያስገባ ነው። የተነሳንለት አላማ ገቢን ማሰባሰብ ባይሆንም ከምንሰጠው አገልግሎት ገቢን በማመንጨት ላይ ነን። ከዚህ በሚገኘው ገቢም ያለንን ፋሲሊቲ በማዘመን የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት እናውለዋለን። ከሌሎች ጋር ያለንን ኔት ወርክ እናስፋፋበታለን።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- በዘርፉ ወደፊትስ ምን ለመስራት አቅዳችዋል?***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** ወደፊት ለመስራት ከያዝናቸው እቅዶች መካከል ዋና ዋናዎቹ እራሳችንን በጥልቀት ማየት፣ ያለንን ፋሲሊቲ መፈተሽ፣ ዙሪያችንንና አካባቢያችንን መቃኘት፣ የአፍሪካንም ሆነ የዓለምን ሁኔታ በመገንዘብ እና አካሄዳችንን በዚያ መልኩ መቃኘት እና አገልግሎቶቻችንን አዘምነን ጥሩ አገልግሎት መስጠት ቀዳሚው ስራችን ይሆናል። ከዚሁ ጋር አያይዘን የደንበኞቻችንን ፍላጎት በመለየትና ፍላጎታቸውን በሚያረካ መልኩ አገልግሎታችንን ማቅረብ ላይ አተኩረን እንሰራለን።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ :- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ዕድሉን ልስጥዎ።***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** በመጨረሻ ማለት የምፈልገው ነገር እንደሀገር ስናየው የስልጠና ጥቅሙ በትክክል አይታወቅም ለማለት እችላለሁ። እንደተቋምም እንደ ግለሰብም የስልጠና ዓላማ ወደ ውስጥ ሰርጾ አልገባም ። የማማከር ስራም እንደ ስርዓት ፍንትው ብሎ እንዲወጣ መስራት ያስፈልጋል። በብዙ ተቋማት ዘንድም ይህ የማማከር አገልግሎት ጠቀሜታ በስፋት አይስተዋልም። ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ስንቃኝ ደግሞ ለስልጠናና ለማማከር አገልግሎት ተቋማት በጀት እንኳን የማይዙበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህን ለመቀየር እና በተቋማት ዘንድ ለዚሁ ዓላማ በጀት የሚያዝበት ሁኔታ እንዲኖር ለመስራትም አስበናል። ስልጠናና ማማከር በሁሉም ዘርፍ ያለውን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ እና በስልጠናና ማማከር ሀገርንም ሆነ ግለሰብን እንደሚለወጥ ያለው ግንዛቤ ሊገዝፍ ይገባል። ይህን የማድረግ ተግባር ደግሞ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በዋናነት የሚጠበቅ ቢሆንም ከእኛም እንዲሁም ከሌሎችም ተቋማት የሚጠበቅ ተግባር ነው። ለዚህም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በግቢያችን Competency Framework Institute ሊያቋቁም በዝግጅት ላይ ነው ። ይህ ለዓላማችን ስኬት አንድ ግብዓት ነው።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲና አሁን ካሉት የስልጠና ማዕከላት ባሻገርም በፌዴራልም ሆነ በክልል በርካታ የስልጠናና ማማከር ማዕከላት ሊኖሩ ይገባል። የስልጠና ማዕከላት በበዙ ቁጥር መልካም አጋጣሚዎች እየሰፉ ይሄዳሉ። ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊየን ሲቪል ሰርቫንት አሏት። እነዚህን ሲቪል ሰርቫንቶች በጥቂት ተቋማት መድረስ አይቻልም። ስለዚህ በአስተሳሰብ መያያዝ፣ በአስተሳሰብ ላይ የተሰመሩትን ከፋፋይ ድንበሮች በማፍረስ፣ ራስን በማልማትና በጋራ በመሆን እንደሀገር ብቻ ሳይሆን እንደአፍሪካም ትልቅ ስራ መስራት ያስፈልጋል። እንደ አፍሪካ አንድ አይነትና ወጥነት ያለው የስልጠና ፕሮግራም ቀርፀን በአፍሪካ ደረጃ ተግባራዊ እናድርግ በማለት በአፍሪካ ሕብረት አማካይነት የተጀምረና እኔም የምሳተፍበት አፍሪካን ማኔጅመንት ኤንድ ዲቨሎፕመንት የሚባል አንድ ኔት ወርክ አለ። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ጎልቶ በመውጣት በአፍሪካ ደረጃ በስፋት ተግባራዊ ቢደረግ ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል። እንዲህ አይነት ወጥነት ያለውና ብዝሀነትን ማስተናገድ የሚችል አካሄድ ካልተለመደና ካልተተከለ ሁሉም ነገር የወሬ አውድማ ሆኖ ይቀራል። ስለዚህ የወሬ ብቻ ሳይሆን የተግባርም፣ የውጤትም ሰው መሆን ይጠበቅብናል። የምንለውን በተግባር ሆነን በመገኘት ጠንካራ ተቋማትን መገንባት አለብን ለማለት እወዳለሁ።

***ዓ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- ዶ/ር ዋቅጋሪ ነገሪ ስለነበረን ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን።***

**ዶ/ር ዋቅጋሪ:-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም

የሀገራችን ኢኮኖሚ ላለፉት 15 ዓመታት በሁለት አኃዝ ሲያድግ እንደነበር በተለያየ መልኩ ሲገለጥ ቆይቷል፡፡ ይህ የሁለት አሀዝ እድገት የራሱ የሆነ ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንደነበሩትም ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ጥንካሬዎቹ በዋናነት የመንግሥት ኢንቨስትመንት ካፒታል ወይም ሀብት በማፍራት ላይ አተኩሮ የተሰራው ስራ ካስገኘው ውጤት ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎች ሲሆኑ እንደድክመት የሚነሱት ደግሞ የግሉን ዘርፍ በበቂ ሁኔታ አለማሳተፍ፣ የፍትሀዊነት ጉድለትና ለልዩ ልዩ ምዝበራዎች የተጋለጠ መሆኑን ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚህ ድክመቶች ከጥቂት ዓመታት በፊት ተፈጥሮ ከነበረው ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ጋር በመሆን እንደ ሀገር አጠቃላይ ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው እሙን ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሀገሪቱ እየተተገበረ ያለውን ይህን ለውጥ ተከትሎ እንደ ሀገር የኢኮኖሚያዊ ሪፎርም ማካሄድ አስፈላጊነቱ በእጅጉ እንደሚጎላ የተለያዩ ምሁራን እና የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ሲለግሱ ቆይተዋል፡፡ ፖለቲካዊ ሪፎርም ከኢኮኖሚው ጋር አብሮ ተያይዞ መሄድና የህብረተሰቡን ችግር መቅረፍ ብሎም የሀገሪቱን አጠቃላይ ዕድገት ሊያፋጥን በሚችልበት መልኩ የተቃኘ የኢኮኖሚ ስርዓት ለውጥ ወይም ማሻሻያ እንዲኖርም ይመክራሉ፡፡ ሀገሪቷ እንደሀገር ከገባችበት ከባድ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ችግር የምትላቀቅበት እና ለዚህ ችግር የሚመጥን መፍትሔ ምን ዓይነት መሆን አለበት በሚለው ጥያቄ ላይም የተለያዩ ሀሳቦችን በመሰንዘር በሀገሪቱ መጻኢ ዕድል ላይ የየራሳቸውን ሀሳብ ሲለግሱ ቆይተዋል፡፡ በቅርቡም ይህን ችግር ለመወጣት ያስችላል የተባለ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ተረቆ ቀርቧል፡፡

የዚህን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ምንነትና ዓላማ አስመልክቶ ከምጣኔ ሀብት ባለሙያውና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዴቨሎፕመንት ኢኮኖሚ መምህርና ተመራማሪ ከሆኑት ከዶ/ር ደሳለኝ ሻሜቦ ጋር ባደረግነው ውይይት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርሙን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየገጠመን ያለውንና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማነቆዎችን ለማስወገድ ትልቅ ሚና ሊጫወት የሚችል ሪፎርም መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡ እንደ ዶ/ር ደሳለኝ ገለጻ ሀገሪቾን ላለፉት 80 ዓመታት ስትከተል የነበረውን የኢኮኖሚ ስርዓት ብንመለከት በንጉሱ ጊዜ የቅይጥ ኢኮኖሚ ስርዓትን ትከተል ነበር፡፡ ይህም ስርዓት የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ተሳትፎ የሚያጎላ ነበር፡፡ በመቀጠል በወታደራዊው የአገዛዝ ስርዓት ወቅት /ምንም እንኳን በመጨረሻ ላይ ወደቅይጥ ኢኮኖሚ ቢለወጥም/ የኢኮኖሚ ስርዓቱ ወደ እዝ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት በመቀየሩ ጠቅላላ የኢኮኖሚው ስርዓቱ ምርትን፣ አቅርቦትን፣ ዋጋን ወዘተ. ጨምሮ የሚቆጣጠረው መንግስት ነበር፡፡ በመቀጠልም ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሲመጣ የገበያ መር ኢኮኖሚ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ተሞከረ፡፡ በዚህ ኢኮኖሚ ስርዓት ደግሞ ትልቁን ሚና መጫወት አለበት የሚባለው የግሉ ዘርፍ ነው፡፡ በገበያ መር አስተሳሰብ ገበያው መመራት ያለበት በፍላጎትና አቅርቦት ላይ ተመስርቶ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ የመንግስት ሚና በግሉ ዘርፍ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ላይ ማተኮርና በእጅጉ የተገደበና ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ እጁን ማስገባት የለበትም የሚል አስተሳሰብ ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሰረት የመንግስት ኃላፊነት የሚሆነው የህግ የበላይነትን ማስከበር ላይ ይሆናል፡፡

ዶ/ር ደሳለኝ እንደሚያብሩት ከ1997 ዓ.ም በኋላ በሀገሪቷ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ስርዓት ለውጥ የተደረገ ሲሆን ቀደም ሲል ከነበረው የገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት ወደ ልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ሽግግር ተደርጓል፡፡ ይህ ልማታዊ መንግስት ከገበያ መር አስተሳሰቦች አንዱ እና ከነጮ ካፒታሊስም አስተሳሰብ በተለየ መልኩ የመንግስትን ተሳትፎ በኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ እንዲኖር የሚፈቅድ የኢኮኖሚ ስርዓት ነው፡፡ ይህም ገበያ በራሱ ሁሉን ነገር መፍታት ስለማይችልና ክፍተት ስላለበት፣ የግል ዘርፉ በማይገባባቸው የልማት መስኮች ላይ መንግስት መግባት እና

በእነዚህ ዘርፎችም ላይ ቀድሞ በመሄድ ለግል ዘርፍ መንገድ መጥረግ ይኖርበታል የሚል አስተሳሰብ ነው የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ። በዚህ ስርዓት ሁለቱ አካላት ማለትም መንግስትም ሆነ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ላይ የጎላ ሚና ይኖራቸዋል።

የእነዚህን የኢኮኖሚ ስርዓቶች በተመለከተም የትኛው የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል የሚለው ጉዳይ አከራካሪና ምሁራን አሁንም የሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ መሆኑን የጠቆሙት ዶ/ር ደሳለኝ እንደ እርሳቸው አመለካከት ግን የገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት ያደገውን ዓለም በይበልጥ የሚጠቅምና በማደግ ላይ ላሉት ሀገራትን ግን እምብዛም የማይረዳ የኢኮኖሚ ስርዓት ነው ይላሉ። ዓላማውም አሁን ያለውን የዓለም ኢኮኖሚ ሚዛን ማስጠበቅ ነው። ስለዚህ ለአደጉት ሀገራት የልማታዊ መንግስት ስርዓት በጣም አስፈላጊ ነው ይላሉ። ያደጉት ሀገራትም በመጀመሪያም የኒዮ ሊብራል አስተሳሰብ አልነበራቸውም፡ ፡ ያለፉትም በልማታዊ የመንግስት ስርዓት ውስጥ ሲሆን ለእድገታቸውም መሰረቱ የተጣለው በመንግስታት ነው የሚል አስተሳሰብ ነው። በምስራቅ ኢስያ የሚገኙ ሀገራትም ዛሬ ላይ ያደጉት ይህን አስተሳሰብ በመከተል ነው።

ነገር ግን በሀገራችን የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ እንደ ምስራቅ ኢስያ ሀገራት ከፍተኛ ውጤት ሊያስመዘግብ ያልቻለበትን ምክንያት ተጠይቀው ሲመልሱ ልማታዊ መንግስት በራሱ ሊኖሩት የሚገቡ መሰረታዊ ባህሪያት እንዳሉት ይጠቅሳሉ። እነዚህ ባህርያትም ጠንካራ የመንግስት ስርዓት እና ጠንካራ የሀገር ወዳድነት ስሜት ናቸው። በእነዚህም ሀገራት በህዝቡ ዘንድ ጠንካራ የሆነ የሀገራዊ ስሜት ከመኖሩ በተጨማሪ ጠንካራና ቁርጠኛ የሆነ ፣ ሀገር ወዳድና ሙስናን አጥብቆ የሚጸየፍ፣ ከራስ በላይ ለሀገር የሚያስብ መንግስት በመኖሩና እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በመሟላታቸው ምክንያት የልማታዊ መንግስት አስተሳሰቡ የተፈለገውን እድገት ሊያመጣ ችሏል ብለዋል።

ከዚህ አንጻር የሀገራችንን መንግስት ስንመለከተው የሚከተለው የፖለቲካ ስርዓት በብሔር ብሄረሰቦች ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ የተነሳ በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ የሚፈለገው ውጤት ሊመዘገብ አለመቻሉንና የፖለቲካ ስርዓቱም ሀገራዊ ስሜት የቀዘቀዘበት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያልሰፈነበት፣ ሙስና በእጅጉ የተስፋፋበት ስርዓት በመሆኑ የታለመው ግብ ሊሳካ አለመቻሉንም አስረድተዋል።

ያም ሆኖ ግን ባለፉት አስራ አምት ዓመታት የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ በመተግበራችን የተለያዩ ለውጦች ተመዝግበዋል ። ለአብነት ያህልም የመንግስት ሪፖርት እንደሚያሳየው ኢኮኖሚው ለተከታታይ ዓመታት በሁለት አሀዝ አድጓል፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ ጨምሯል፤ የእናቶችና የህጻናት ሞት ቀንሷል፤ የዜጎች የመኖሪያ ዕድሜ ጨምሯል። በአጠቃላይ ድህነትን በአስራ አምስት በመቶ ለመቀነስ ተችሏል። ነገር ግን ሀገሪቷ ከነበረችበት የከፋ ድህነት አንጻር ሲታይ የመጣው እድገት እዚህ ግባ ሊባል የሚችል አለመሆኑንም አክለውበታል።

በእነዚህ ዓመታት ስለተመዘገበው ለውጥ ሲያስረዱም በዋናነት ምክንያት የሚሆነው የመንግስት የተለጠጠና በከፍተኛ ወጪ የተደረገ ኢንቨስትመንት ነው ብለዋል። ይህ የተለጠጠ ኢቨስትመንት የኮንስትራክሽንና የአገልግሎት ዘርፉን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲነቃቃ አድርጎታል። ይህን ለማሳካትና የመንግስትን ወጪ ለመሸፈን ቁጠባን በማበረታታት ቅድሚያ ለተሰጣቸው የልማት ዘርፎች ለማዋል ተሞክሯል ። ለአብነት ያህልም በ2010 ዓ.ም ከአጠቃላዩ GDP ሃያ አራት በመቶ ቁጠባ ተመዝግቧል። ከዚህ በተጨማሪም ከውጪ የሚገኘው ዕርዳታና ብድርም ለመንግስት ኢንቨስትመት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ነበረው። ምንም እንኳን ወደ ከፍተኛ የብድር ጫና ውስጥ ብንገባም፤ የብድር መጠኑም ጣራ ነክቶ ከፍተኛ ባለዕዳ ብንሆንም በብድር የመጣው ገንዘብ ወደ ልማቱ በማስገባት ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት ተሞክሯል። ሌላው ለመጣው ለውጥ የኢንቨስትመንት እድገት አስተዋጽኦ ያበረከተው የኔጋቲቭ ኢንተረስት ሬት ነው። ባለፉት አስራ አምስት አመታት ውስጥ በሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት ተከስቷል። ይህም በሰዎች ዘንድ ገንዘብን ከመያዝ ይልቅ ወደ ኢንቨስትመንቱ እንዲገቡና አሴት እንዲይዙ ነው ያደረገው።

ነገር ግን ይህ ዕድገት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የራሱ የሆነ ማነቆዎችና ተግዳሮቶች እየገጠሙት መጥተዋል፡ ፡ እንደሚታወቀም ሀገሪቷ በ2025 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ አቅዳ በመስራት ላይ ትገኛለች። ይህን እንቅስቃሴ ስንገመግመው በትምህርትና በጤና ዘርፉ ያለንበት ደረጃ በጣም ጥሩ ከሚባል ደረጃ ላይ ቢሆንም የነፍስ ወከፍ ገቢን ከማሳደግ ፣ ድህነትን ከመቀነስ ፣ የኤሌትሪክና የንጹህ ውሃ አቅርቦትን ከመጨመር እና ከመሳሰሉት አንጻር በጣም ወደኋላ ቀርተናል።

ከሁሉም በላይ የነበረው ዕድገት የመዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ያልቻለ እድገት ነበር ለማለት ይቻላል። የኢኮኖሚው መሰረት ከሆነው ግብርና በሂደት እየቀነሰ የአምራች ዘርፉና የአገልግሎት ዘርፉ ሊተካ ይገባው ነበር። ከዚህ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የመዋቅር ለውጥ ማምጣት ያልቻለ አካሄድ ነበር። በአጠቃላይ

ሲታይም ባለፉት አመታት የመጣው የኢኮኖሚ ዕድገት በሀብት ክምችት ማለትም መንግስት ተበድሮ ባመጣቸው ውስን ስራዎች ላይ የተመሰረተ እንጂ ከኢኮኖሚው የመነጨ ዕድገት አልነበረም። ለዚህ ነው አንዳንድ ኢኮኖሚስቶች በምርታማነት የመጣ ዕድገት አይደለም የሚሉት። ትክክለኛና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚመነጨው ግን ምርታማነትን በማሳደግ ነው።

ከዚህ አኳያ ሲታይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁለት መሰረታዊ ማነቆዎች እንዳሉበት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ማነቆዎቹን ለማስወገድ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ዶክመንት መዘጋጀቱን ዶ/ር ደሳለኝ ያብራራሉ። እነዚህ ማነቆዎችም የመጀመሪያው መዋቅራዊና ተቋማዊ ማነቆ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ናቸው።

የዶክመንቱን አጠቃላይ ይዘት ሲያብራሩም በሀገሪቷ በመዋቅራዊና ተቋማዊ ድክመቶች የተነሳ ምርታማነትን የማሳደግ ችግር መኖሩን በዶክመንቱ መዘርዘሩን አመልክተዋል። የአለም ኢኮኖሚክስ ፎረም እና የUNDP ሪፖርት እንደሚያሳየው የውጪ ምንዛሪ አስተዳደርና አቅርቦት ደካማ መሆን፣ የፋይናስ አስተዳደርና አቅርቦት ደካማነት ፣ የኤሌትሪክ ኃይል አስተዳደርና አቅርቦት በጣም ዝቅተኛ መሆን ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ውሱንነት፣ ሙሰኝነት የተስፋፋበትና የተንዛዛ የመንግስት ቢሮክራሲ እና ደካማ የሆነ የኢንተርኔት አገልግሎች የኢኮኖሚው ማነቆዎች መሆናቸው በዶክመንቱ ተገልጿል። ከእነዚህ በተጨማሪም በአምራችና የአገልግሎት ዘርፉ ላይም በርካታ ችግሮች ነበሩ፡ ፡ እምቅ የሆኑት የሀገሪቷ ሀብት ግብርና፣ ማኑፋክቸሪኒግ ማዕድንና ቱሪዝምን እንዳያድግ እነዚህ መዋቅራዊና ተቋማዊ ማነቆ አግደውታል በማለት ዶክመንቱ ያብራራሉ።

ሌላውና ሁለተኛ ማነቆ ስለሆነው የማክሮ ኢኮኖሚው መዛባት ዶ/ር ደሳለኝ ሲያብራሩ ባለፉት አስራ አምስት አመታት የነበረው ዕድገት የማክሮ ኢኮኖሚው መዛባትን ያስከተለ ያስከተለ መሆኑን ጠቅሰው በመንግስት የሚደረጉ ሰፋፊ ኢንቨስትመንቶችና ፕሮጀክቶች ላይ በቂ የሆነ የአዋጭነት ጥናት ካለመደረጉም በተጨማሪም ፕሮጀክቶቹን ሊመራ የሚያስችል የሰው ኃይልና የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖሩን ገልጸዋል። በዚህ የተነሳም ፕሮጀክቶቹ ስኬታማ አልነበሩም፡ ፡ በዚህ ረገድ ደካማና ዝርክርክ አስተዳደር በመኖሩ የተናሳ መንግስት አንዱንም ማጠናቀቅ ባለመቻሉ ከፍተኛ ብክነት ነበረ። እነዚህን ፕሮጀክቶች ለማስኬድ በርካታ የውጪ ምንዛሪ አስፈልጓል። በዚህ የተነሳ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ተከትሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከፍተኛ የሆነ የውጪ ምንዛሪ እጥረት ተከስቷል። ከዚህም ሌላ ሀገሪቷ ከፍተኛ የሆነ የዕዳ ጫና ውስጥ እንድትገባ አስገድዷል። ወደ ሰላሳ ቢሊየን ዕዳ የተሸከመች ሀገር ሆናለች። በሶስተኛ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረትም ተከስቷል ። ባለፉት ዓመታት በየዓመቱ በአስራ አምስት በመቶ የሆነ የዋጋ ንረት ተመዝግቧል። በአራተኛ ደረጃ ለግሉ ዘርፍ ይውል የነበረውን የብድር አገልግሎት መንግስት እራሱ ተበዳሪ በመሆኑ የተነሳ በአግባቡ ለግሉ ዘርፍ እንዳይደርስ ውሱንነት አስከትሏል ። በዚህም የተነሳ



**ከዶ/ር ደሳለኝ ሻሜቦ**
*ምጣኔ ሀብት ባለሙያና መምህር*

ጠንካራና ተፎካካሪ የሆነ የግሉ ዘርፍን መፍጠር ያላስቻለ የኢኮኖሚ እድገት ነበር። የነበሩትም ባለሀብቶች ጥገኛ የነበሩ ከመንግስት አካላት ጋር በአንዳች መልኩ የተገናኙ እንደነበሩም ዶ/ር ደሳለኝ አስታውሰዋል።

ከዚህ በመነሳት የነበረው ዕድገት ከፍተኛ የሆነ የንግድ ሚዛን ጉድለት ያስከተለ ነበር። ይህ ደግሞ ኢንቨስትመንቱን መልሶ ጎድቶቷል። ከዚህም ባሻገር እያደገ በመጣው በከፍተኛ የብድር ጫና ውስጥ እንድትዘፈቅ በማድረጉ፤ ተጨማሪ ብድር እንኳን ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲፈጠር ሆኗል። በሌላ በኩል መንግስት እራሱ ተበዳሪ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ እንዲጎዳ ሆኗል። ሌላው ልቅ የሆነው (expansionary) የፋይናንስና የሞኒታሪ ፖሊሲ መኖር የዋጋ ንረቱን በማስከተል በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች ከፍተኛ ጫናን የፈጠረ ዕድገት ነበር። ስለዚህ ይህን ችግር ለመፍታት በማሰብ ነው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ሰነድ የተዘጋጀው ብለዋል።

ሪፎርሙም ሀገር በቀል የተሰኘበት ምክንያት ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት እና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት ነባራዊ ሁኔታዎችን መሰረት አድርጎ የተነሳ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመሆኑ ይመስላል ያሉት ዶ/ር ደሳለኝ ሪፎርሙን በዝርዝር ስንመለከተው በዋናነትም ከላይ የተገለጹትን መዋቅራዊና ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የተዘጋጀ እና ወደ ንጹህ የገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት መሄድ አለብን የሚል ሀሳብን ያዘለ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ነው ብለው እንደሚወስዱት ገልጸዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ማሻሻያው ሪፎርሙ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ ተቋማዊና መዋቅራዊ ማሻሻያ እና ሴክተራል ማሻሻያ ናቸው፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና አላማ ቀደም ሲል የታየውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ማስተካከል ሲሆን ለዚህም የተረጋጋ የፊሲካልና የፋይናንስ ስርዓትን በማስፋፋት፣ ዕድገትንና የስራ ዕድል ፈጠራን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህን ሪፎርም ለመተግበርም የሚከተሉት እርምጃዎች (sub reforms ) አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ የመጀመሪያው እርምጃ የፐብሊክ ፋይናንስ ሪፎርም ሲሆን ይህም ወቅቱን ያገናዘበ የፊሲካል ፖሊሲን መተግበር ነው፡፡ ይህም የታክስ ስርዓቱንና ገቢን ማሻሻል፣ የመንግስት ኢንቨስትመንትን ውጤታማነት ማሻሻል፣ የመንግስት የልማት ዘርፎችን ወደግሉ ዘርፍ ማዞር፣ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የአሰራር ስርዓትን ውጤታማነትን፣ ግልጽነትንና አስተዳደሩን ማሻሻልን ያካትታል፡፡

ሁለተኛው ማሻሻያ ደግሞ የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት ችግርን መቅረፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን የሚገኘውን የውጪ ምንዛሬ መጠን ማሳደግና የተገኘውን የውጪ ምንዛሬ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግን ያካትታል፡፡ በዚህም መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ማዞርና የውጪ ምንዛሪን ማግኘት፣ ረጅም የችሮታ ጊዜና ጫና የማይፈጥሩ ብድሮችን መበደር፣ መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን በመተግበር የውጪ ንግድን፣ ቱሪዝምን፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ማሻሻልና ማጠናከር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተጨማሪም ዲያስፖራን ያካተተ ቁጠባን ማጠናከር፣ ለግሉ ዘርፍ አስመጪዎች የውጪ ምንዛሪ አቅርቦትን ማጠናከር፣ እንዲሁም የውጪ ምንዛሬ ገበያ አሰራርን ማሻሻልን የያዘ ሪፎርም ነው፡፡

ሶስተኛው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ማሻሻያ የሆነው ከፍተኛ የሆነውን የዋጋ ንረትን መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ማሻሻያ ሲሆን ይህም የገንዘብ ፖሊሲ አተገባበር ማዕቀፍን ማሻሻልና የኑሮ ውድነቱን መቋቋም የሚያስችል የገንዘብ ፖሊሲ መጠቀም ላይ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዚህም ውጤታማ የሆኑ የገንዘብ ፖሊሲዎችን መተግበር፣ የብሔራዊ ባንክን የትንተና አቅም ማሻሻል፣ የሀገር ውስጥ የግብይት ስርዓትን ማሻሻል እና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ ማሻሻያ ነው፡፡

አራተኛው የባንኮችን የአሰራር ስርዓት ማሻሻልና ማዘመን ላይ የሚሰራና የብሔራዊ ባንክን አሰራርና ቁጥጥር በማሻሻልና በማዘመን የተረጋጋ የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማስቻልን ማዕከል ያደረገ ሲሆን አምስተኛውና የመጠረሻው ማሻሻያ ደግሞ የአገር ውስጥ ቁጠባን በማሳደግና የፋይናንስ ተደራሽነትን በማጎልበት፤ የፋይናንስና የካፒታል ገበያ መፍጠር ላይ ያተኮረ ማሻሻያ ነው፡፡ ይህም ሪፎርም ጠንካራ፣ ተወዳዳሪና የተሳለጠ የግምጃ ቤት ሰነድን ለመሸጥ ፣ የቦንድና የአክስዮን ገበያን እንዲኖር ለማድረግ ያለመ ማሻሻያ ነው፡፡

እነዚህ አምስቱ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል የተቀረጹ ንዑስ ማሻሻያዎች ውጤታማ የሚሆኑት መዋቅራዊ ማሻሻዎቹ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን በመፍጠር እገዛ ሲያደርጉ ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት የማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች ለመተግበር መዋቅራዊ ለውጦችን ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሁለተኛው የሆነው ማሻሻያ ማለትም ተቋማዊና መዋቅራዊ ማሻሻያ ተቀርጿል፡፡ ይህ መዋቅራዊ ማሻሻያ በውስጡ የቢሮክራሲና የቁጥጥር ስርዓትን ማሳለጥ፣ በመንግስት ተቋማት መልካም አስተዳደርን በተግባር ማስፈን፣ የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦትን ማሻሻል፣ በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፣ በውጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች አስተማማኝ ገበያን በመፍጠር የውጪ ንግድን ማበረታታት፣ የኢትዮጵያን ንግድ መርከብና ሎጂስቲክ አሰራርን ቀልጣፋ ማድረግ እንዲሁም ቀልጣፋ የሀገር ውስጥ የገበያ ስርዓትን መዘርጋትን ያቀፈ ማሻሻያ ነው፡፡

ሶስተኛው ሪፎርም ሴክተራል ሪፎርም የሚባለው ነው፡ ፡ ይህ ማሻሻያ በዋናነት የሚያተኩረው ሀገራችን በግብርና በማዕድን፣ በቱሪዝምና በአምራች ዘርፉ ላይ ያላትን እምቅ አቅም ማሳደግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ግብርና በመደገፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አነስተኛ መሬት ላይ ያሉ ገበሬዎችን መደገፍ፤ ሰፋፊ እርሻዎችም በአክስዮን በኢንቨስትመንት

እንዲሰሩ ማድረግ፣ የእንስሳት ግብርናን ማሳደግና የገበያ ትስስርን መፍጠር፣ አግሮ ኢንዱስትሪዎችንና መስኖን ማስፋፋት፣ ለግብርናው ዘርፍ የሚያገለግሉ የፋይናንስ አገልግሎቶች በዋናነት የብድርና የኢንሹራንስ አገልግሎትን አቅርቦትን ማዕከል ያደረገ ነው። በማምረቻ ዘርፉም ያሉትን የማበረታቻ ስርዓቶች መመርመርና ማሻሻል፣ የሀገር ውስጥ ግብዐቶችን ለሚጠቀሙ ቅድሚያ መስጠትና መደገፍ፣ የኢንዱስትሪዎችን ትስስር ማጠናከር፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ አምራቾችን በከፍተኛ ደረጃ መደገፍ፣ ለሰራተኞች ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኙና የኢንዱስትሪውን ሰላም እና የስራ ላይ ደህንነትን ማስጠበቅና የሰራተኛ ፍሰትን መቀነስ ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።

የማዕድን ዘርፉን በተመለከተም በባህላዊ መንገድ የሚደረጉትን በማሻሻል ወደ ህጋዊው አሰራር እንዲገቡ ማድረግ፣ በዘርፉም በተለይ በወርቅ ማምረቻዎች አካባቢ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣ የማዕድን አምራቾችን ቴክኒካዊና መዋቅራዊ ተግዳሮቶችን መፍታትና የጂዎሎጂካል መረጃዎችን በአግባቡ ማጠናቀርና መጠቀምን የሚያበረታታ ሲሆን በቱሪዝም ዘርፉ ዙርያም የቱሪስት ስፍራዎችንና ታሪካዊ ቦታዎችን ማራኪና ተደራሽ ማድረግ፣ የቱሪዝም አገልግሎቱን ማዘመን፣ አዳዲስ የቱሪስት ማዘውተሪያ ቦታዎችን ማልማት፣ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች የሀገር ውስጥ ግብዐቶችን እንዲጠቀሙ በማድረግ ከሀገር ውስጥ አምራቾች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ፣ አዳዲስ የስራ ፈጠራ ምንጮችንም ማፈላለግና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ማጠናከር ላይ ያተኮረ ሪፎርም ነው።

በዚህ መልክ የሪፎርሙን ዝርዝር ያብራሩልን ዶ/ር ደሳለኝ ስለተግባራዊነቱ ተጠይቀው ሲመልሱ የሪፎርሙ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ያተኮረ መሆኑንና ዘላቂ እድገትን፣ የስራ ዕድል ፈጠራን ማጠናከር ላይ ያለመ መሆኑን አስታውሰው ሪፎርሙን ለመተግበር ግን ከባድ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን አመላክተውል። እንደ ዶ/ር ደሳለኝ ማብራሪራ ፕላኑን ለማውረድ ጠንካራ የሆነ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እጅግ አስፈላጊ ነው። በዜጎች ዘንድም ጠንካራ የሆነ ሀገራዊ ስሜት መፈጠር አለበት። ሪፎርሙ እንዲተገበር ዜጎች ወደየትኛውም የሀገሪቷ ክፍል በነጻነት በመንቀሳቀስ መስራትና ሀብት ማፍራት አለባቸው። የመንግስት መዋቅሩም ጠንካራና ቁርጠኝነትን የተላበሰ፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነበት፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሆነ፣ ከፖለቲካዊ ሹመት ባሻገር በሙያ ላይ የተመሰረተና የአገልጋይነት መንፈስን የተላበሰ ቢሮክራሲ መመራት ይገባዋል። በሀገሪቷ ያለውን ከፍተኛ የሆነ የሰው ሀብት በአግባቡ በመጠቀምና ተገቢው ሙያተኛ በተገቢው ቦታ ላይ በመመደብ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ጠንካራ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምን መተግበርም አስፈላጊ ይሆናል። ስነምግባር ያለው፣ ሙስናን የሚጸየፍ፣ ሀገር ወዳድ የሆነ ብቃት ያለውና ሜሪት ቤዝድ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ ያስፈልጋል። ሪፎርሙን ለመተግበርም ፋይናስና ሀገራዊ ሰላምን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ስራ መሰራት ይኖርበታል።

እንደግለሰብ ሲታይ ደግሞ ያለን አንድ ሀገር በመሆኑ መላው ማህበረሰብ ከምንም በላይ የሀገር ወዳድነት ስሜትን በመላበስ ለሀገሩ ቅድሚያ በመስጠት ሊሰራ ይገባል። ሀገሪቷን ሊለውጡ የሚችሉ በዓለም ዙሪያ የተበተኑ ኢትዮጵያውያንን ወደሀገራቸው በመግባት ለሀገር እድገት በጋራ መስራት ላይ ትኩረት ማድረግ በሁሉም ወገን ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ሀገር የሚለወጠው በስራ ብቻ መሆኑን እና የሀገሪቷም የወደፊት ዕጣ ፈንታ በእጃችን መሆኑን በመገንዘብ ከፖለቲካ ጨዋታ በመውጣት ጠንካራና ሀገር ወዳድ ዜጋ በመሆን ከችግሮቻችን ተምረን ለሀገር እድገት መስራት በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን የገለጹት ዶ/ር ደሳለኝ በዚህ መንፈስ ተቃኝተን ሁላችንም ከተጋን ሪፎርሙን በመተግበር ሀገራችንን ወደ ታለመው የብልጽግና ደረጃ ማድረስ እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.lprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University




BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995